- ማንም።

- ከእስራኤላውያን መካከል የሞተ ነበር?

ዘጸአት 14፡29-30

29- እስራኤላውያን ግን ውኃው ግራና ቀኝ እንደ ግድግዳ ሆኖ፣ በደረቅ ምድር ባሕሩን ተሻገሩ።

30- በዚያች ዕለት እግዚአብሔር እስራኤልን ከግብፃውያን እጅ አዳናቸው፤ እስራኤልም የግብፃውያን ሬሳ በባሕሩ ዳርቻ ወድቆ ተመለከቱ።

- አንድም እስራኤላዊ አልሞተም።

- አንድም እስራኤላዊ ያልሞተው ለምን ነበር?

- ምክንያቱም እግዚአብሔር ስለጠበቃቸው ነው።

- እግዚአብሔር እስራኤላውያንን የጠብችቃቸው ለምንድን ነው?

- እግዚአብሔር እስራኤላውያንን የጠበቃቸው ከአብርሃምና ከእስራኤላውያን ዘር አዳኝ እንደሚልክ ቃል ስለ ገባ ነው።

- እግዚአብሔር እስራኤላውያንን የጠበቃቸው ደግሞ፥ ቃሉን ማለትም መጽሐፍ ቅዱስን በአብርሃምና በእስራኤላውያን አማካይነት ወደ ዓለም ሕዝቦች ሁሉ ለመላክ ስለ ፈለገ ነው።

- በእግዚአብሔር ብናምን እግዚአብሔር ያድነናል።

- በእግዚአብሔር ካላመንን እግዚአብሔር አያድነንም።



ትምህርት 30

1. እግዚአብሔር ዘጠኝ አስፈሪ መቅሰፍቶችን በፈርዖንና በግብፃውን ላይ ቢያወርድባቸውም እንኳን ፈርዖን እስራኤላውያንን ለቀቃቸው?

ሀ- አልለቀቃቸውም።

2. እግዚአብሔር በመጨረሻው የላከው መቅሰፍት ምን ነበር?

ለ- የመጨረሻው መቅሰፍት የግብፃውያንን ልጆችና ከብቶች በኩር የሚገድል መቅሰፍት ነበር።

3. እያንዳንዱ የእስራኤላውያን ቤተሰብ ባል የበኩር ልጁ እንዳይሞት ምን እንዲያደርግ እግዚአብሔር አዘዘው?

ሀ- የአንድ ዓመት የበግ ወይም የፍየል ጠቦት እንዲመርጥ።

4. የበኩር ልጆቻቸው እንዳይሞቱ እስራኤላውያን እንዲመርጡ እግዚአብሔር ያዘዘው በግ ወይም ፍየል ምን አይነት ነበር?

ሀ- ምንም ነውር የሌለበት።

5. ለምንድን ነው እግዚአብሔር የአንድ ዓመት የበግ ወይም የፍየል ጠቦት ነውር የሌለበት እንዲሆን ያዘዘው?

ሀ- እግዚአብሔር ፍጹም ስለሆነ ነው።

ለ- እግዚአብሔር የሚናናገረው ነገር ሁሉ ፍጹም ስለሆነ ነው።

ሐ- እግዚአብሔር የሚያደረገው ነገር ሁሉ ፍጹም ስለሆነ ነው።

6. እግዚአብሔር በወሩ በአሥራ አራተኛው ቀን ጠቦቱን ምን እንዲያደርጉ አዘዛቸው?

ሀ- እግዚአብሔር ጠቦቱ እንዲታረድ አዘዘ።

ለ- እግዚአብሔር ጠቦቱ እንዲሞት አዘዘ።

7. እግዚአብሔር ጠቦቱ እንዲሞት ያዘዘው ለምን ነበር?

ሀ- እግዚአብሔር ኃጢአትን የሚቀጣው በሞት መሆኑን ለእስራኤላውያን ለማስተማር ነው።

8. እግዚአብሔር እስራኤላውያን የጠቦቱን ደም ምን እንዲያደርጉ አዘዛቸው?

ሀ- በጎድጓዳ ዕቃ ውስጥ እንዲያስቀምጡት አዘዛቸው።

9. ከዚያስ እግዚአብሔር እስራኤላውያን በጎድጓዳ ሳሕን ውስጥ ያለውን ደም ምን እንዲያደርጉ አዘዛቸው?

ሀ- እግዚአብሔር እስራኤላውያንን በዚያ ምሽት የበጉን ሥጋ የሚበሉበትን ቤት ሁለቱን መቃንና ጉበን እንዲቀቡ አዘዛቸው።

10. እስራኤላውያን ከውጭ ደም በተቀባ ቤት ውስጥ እንዲቆዩ እግዚአብሔር ያዘዛቸው ለምንድን ነው?

ሀ- በውጭ ያለው ደም በውስጥ ያሉትን እስራኤላውያን እንዲሸፍን ነው።

11. እግዚአብሔር እኛ በራሳችን መንገድ ራሳችንን እንድናድን ይፈቅዳል?

ሀ- አይፈቅድም።

12. ሊያድነን የሚችለው ብቸኛ መንገድ የማን መንገድ ነው?

ሀ- የእግዚአብሔር መንገድ ነው።

13. እግዚአብሔር በተናገረው መሠረት የግብፃውያንን በኲሮች ሁሉ ገደለ?

ሀ- አዎን።

14. ከእርሱ የበኲር ልጅ ሞትና ከግብፃውያን በኲራት ሞት በኋላ ፈርዖን ምን አደረገ?



- ፈርዖንና ሠራዊቱ እስራኤላውያንን ተከትለው ወደ ቀይ ባሕር በገቡ ጊዜ እግዚአብሔር ምን አደረገ?

ዘጸአት 14፡24-28

24- ሲነጋጋም እግዚአብሔር በእሳትና በደመና ዓምድ ሆኖ የግብፃውያንን ሠራዊት ቁልቁል ተመለከተ፤ በግብጻውያንም ሰራዊት ላይ ሽብር ላከባቸው።

25- መንዳት እንዳይችሉም የሠረገላዎቹን መሽከርከሪያዎች አቆላለፈባቸው። ግብፃውያኑም፣ «ከእስራኤላውያን እንሽሽ! እግዚአብሔር ግብጽን እየተዋጋላቸው ነው» አሉ።

26- ከዚያም እግዚአብሔር ሙሴን፣ «ውኃው ግብፃውያንን፥ ሠረገሎቻቸውንና ፈረሰኞቻቸውን ተመልሶ እንዲሸፍናቸው እጅህን በባሕሩ ላይ ዘርጋ» አለው።

27- ሙሴም እጁን በባሕሩ ላይ ዘረጋ፤ ንጋት ላይም ባሕሩ ወደ ቀድሞ ቦታው ተመለሰ። ግብፃውያን ከውኃው ሸሹ፤ እግዚአብሔርም ግብፃውያንን በባሕር ውስጥ ጣላቸው።

28- ውኃውም ተመልሶ እስራኤላውያንን ተከትለው ወደ ባሕሩ የገቡትን ሠረገሎች፥ ፈረሰኞች፣ መላውን የግብፅ ሠራዊት ሁሉ ሸፈነ። አንድም እንኳ አልተረፈም።

- እግዚአብሔር ፈርዖንንና ሠራዊቱን በቀይ ባሕር ውስጥ አሰጠማቸው።
- አንድም የፈርዖን ሠራዊት አልተረፈም።

- ፈርዖን ከእግዚአብሔር ጋር ታግሎ ማሸነፍ ችሎአል?
- አልቻለም።

- ከእግዚአብሔር ጋር ታግሎ ማሸነፍ የሚችል ማን ነው?

- ፈርዖንና ሠራዊቱ እስራኤላውያንን መልሰው ለመያዝ በመምጣት ላይ ነበሩ፤ እስራኤላውያንን ለመከላከል እግዚአብሔር ምን አደረገ?

ዘጸአት 14፡19-20

19- ከዚያም ከእስራኤል ሠራዊት ፊት ፊት ሆኖ ሲሄድ የነበረው የእግዚአብሔር መልአክ ተመለሰና ወደ ኋላቸው መጣ፤ የደመናውም ዓምድ እንዲሁ ከፊት ተነሥቶ ከኋላቸው ቆመ፤

20- በግብፅና በእስራኤል ሰራዊት መካከል በመሆን፣ ሌሊቱን ሙሉ ደመናው በአንድ በኩል ጨለማን ሲያመጣ፣ በሌላው በኩል ብርሃን አመጣ፤ ስለዚህ ሌሊቱን በሙሉ አንዱ ወደ ሌላው ሊጠጋ አልቻለም።

- እግዚአብሔር በእስራኤላውያንና በፈርዖን ሠራዊት መካከል ደመናን አደረገ።

- ደመናው ለእስራኤላውያን ብርሃንን ሲሰጥ ለፈርዖንና ለሠራዊቱ ግን ጨለማ እንዲሆን አደረገ።

- ምንም እንኳ ደመናው ለፈርዖንና ለሠራዊቱ ጨለማ እንዲሆን ቢያደርግም እስራኤላውያንን ማሳደዳቸውን አላቋረረጡም ነበር።

- ፈርዖንና ሠራዊቱ እስራኤላውያንን ተከታትለው ቀይ ባሕር ውስጥ ገቡ።

ዘጸአት 14፡23

23- ግብፃውያንም አሳደዷቸው፤ የፈርዖን ፈረሶች፥ ሰረገሎችና ፈረሰኞች በሙሉ ተከትለዋቸው ወደ ባሕሩ ገቡ።



ሀ- ፈርዖን እስራኤላውያን እንዲሄዱ ፈቀደ።

15. ፈርዖንም ሆነ ሌላ ሰው ከእግዚአብሔር ጋር መዋጋትና ማሸነፍ ይችላል?

ሀ- አይችልም።

- እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ከግብጽ ካወጣቸው በኋላ ወደ የትኛው ምድር መራቸው?

- መልሶ ወደ ከነዓን ምድር መራቸው።

- ከነዓን እግዚአብሔር ለአብርሃም ለይስሐቅ ለያዕቆብና ለዘሮቻቸው ቃል የገባላቸው ምድር ነበር።

- እስራኤላውያን በመጀመሪያ ወደ ግብፅ ሲመጡ ሰባ ሰዎች ብቻ ነበሩ።

- በግብፅ ለ400 ዓመታት ያህል ከኖሩ በኋላ ቁጥራቸው ወደ ሁለት ሚሊዮን ደረሰ።

- እግዚአብሔር ሁለት ሚሊዮን የሚደርሱ ሰዎችን የመራው እንዴት ነበር?

ዘጸአት 13፡21-22

21- ስለዚህ በቀንም ሆነ በሌሊት መጓዝ ይችሉ ዘንድ፣ እግዚአብሔር በቀን በመንገዳቸው ሊመራቸው በደመና አምድ፣ በሌሊት ደግሞ ብርሃን ሊሰጣቸው በእሳት አምድ በፊታቸው ይሄድ ነበር።

22- በቀንም ሆነ በሌሊት የደመናውና የእሳቱ ዓምድ ከሕዝቡ ፊት የተለየበት ጊዜ አልነበረም።

- እግዚአብሔር እስራኤላውያንን በቀን የመራው እንዴት ነበር?

- በደመና ዓምድ።

- እግዚአብሔር እስራኤላውያንን በሌሊት የመራው እንዴት ነበር!

- በእሳት ዓምድ።

- እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ባይመራቸው ኖሮ ወዴት መሄድ እንዳለባቸው ያውቁ ነበር?

- አያውቁም።

- እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ባይመራቸው ኖሮ ምን ይደርስባቸው ነበር?

- ይጠፉና ይሞቱ ነበር።

- እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ስለ ወደዳቸው እስራኤላውያን እንዳይጠፉና እንዳይሞቱ መራቸው።

- እግዚአብሔር የቀይ ባሕር እስከተባለው ባሕር ድረስ መራቸው።

- ቀይ ባሕር እንደ ደረሱ እግዚአብሔር እስራኤላውያን እዚያ ለጥቂት ጊዜ እንዲያርፉ ነገራቸው።

ዘጸአት 14፡1-3

1- ከዚያም እግዚአብሔር ሙሴን አለው፤

2- «እስራኤላውያን ተመልሰው በሚግዶልና በባሕሩ መካከል ባለው በፊሀሒሮት አጠገብ እንዲሰፍሩ ንገራቸው፤ በበአል ዛፎንም አንጻር በባሕሩ አጠገብ ይስፈሩ።



- እግዚአብሔር እስራኤላውያን ለማዳን መንገድ አዘጋጅቷል?

ዘጸአት 14፡21-22

21- ሙሴ እጁን በባሕሩ ላይ ዘረጋ፤ እግዚአብሔር ሌሊቱን በሙሉ ብርቱ የምሥራቅ ነፋስ አስነሥቶ ባሕሩን ወደ ኋላ በማሸሽ ደረቅ ምድር አደረገው፤ ውኃው ተከፈተ፤

22- እስራኤላውያን ውኃው በግራና በቀኝ እንደ ግድግዳ ሆኖ በየብስ በባሕሩ ውስጥ አለፉ።

- እግዚአብሔር ቀይ ባሕር እንዲከፈልና እስራኤላውያን በደረቅ ምድር እንዲሻገሩ መንገድ እንዲሰጥ አዘዘው።

- ቀይ ባሕርን መክፈል ለእግዚአብሔር አስቸጋሪ ነበር?

- አልነበረም።

- ቀይ ባሕርን መክፈል ለእግዚአብሔር አስቸጋሪ ያልሆነው ለምን ነበር?

- ምክንያቱም ቀይ ባሕርን የፈጠረው እግዚአብሔር ስለሆነ ነው።

- ምክንያቱም የባሕሩ ሁሉ ጌታ እግዚአብሔር ስለሆነ ነው።

- ምክንያቱም እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ ስለሆነ ሁሉንም ማድረግ ስለሚችል ነው።

- እስራኤላውያን ቀይ ባሕርን ማቋረጥ ጀመሩ።

- ምክንያቱም ቀይ ባሕር ከፊት ለፊታቸው ተራሮች በግራና በቀኛቸው እንዲሁም ደግሞ የፈርዖን ሠራዊት ከበስተኋላቸው ስለነበር ነው።

- እስራኤላውያን ወጥመድ ውስጥ ገብተው ነበር።

- እስራኤላያንን ማዳን የቻለው ብቸኛው ማን ነበረ?
- እግዚአብሔር።

- አዳምና ሔዋን ከኤድን የአትክልት ስፍራ ከተባረሩ በኋላ ወደዚያ መመለስ አልቻሉም ነበር።

- እነርሱ የሚድኑበትን መንገድ ማዘጋጀት የቻለው እግዚአብሔር ብቻ ነው።

- የይስሐቅ እጆችና እግሮች በታሠሩ ጊዜና የአብርሃም ቢላዋ ሊሠዋው በተዘጋጀ ጊዜ ይስሐቅ ራሱን ማዳን አልቻልም ነበር።

- ይስሐቅ የሚድንበትን መንገድ ማዘጋጀት የቻለው እግዚአብሔር ብቻ ነው።

- እስራኤላውያን ወጥመድ ውስጥ ስለገቡ ራሳቸውን ማዳን አልቻሉም።

- እስራኤላውያን የሚድኑበትን መንገድ ማዘጋጀት የቻለው እግዚአብሔር ብቻ ነው።

- እስራኤላውያን የሚድኑበትን መንገድ ማዘጋጀት የቻለው እግዚአብሔር ብቻ እንደሆነ ሁሉ፥ እኛንም ለማዳን መንገድ ማዘጋጀት የሚችለው እግዚአብሔር ብቻ ነው።



3- ፈርዖን “እስራኤላውያን ግራ ተጋብተው በምድረ በዳ በመቅበዝበዝ ይንከራተታሉ” ብሎ ያስባል። »

- እግዚአብሔር እስራኤላውንን እስከ ቀይ ባሕር ዳርቻ ድረስ የመራቸው ለምን ነበር?

- እግዚአብሔር እርሱ ብቻ አምላክ መሆኑን ግብፃውያንም ሆኑ እስራኤላውያን እንዲያውቁ ስለ ፈለገ።

- ፈርዖን ምን እንደሚያስብ ለእግዚአብሔር ማን ነገረው?

- ማንም አልነገረውም።

- ፈርዖን ምን እንደሚያስብ እግዚአብሔር እንዴት አወቀ?

- ፈርዖን ከማሰቡ በፊት እግዚአብሔር የፈርዖንን እያንዳንዱን አሳብ ያውቃል።

- እግዚአብሔር፥ ከማሰባችን በፊት እንኳ፥ የምናስበውን አሳብ ሁሉ ያውቃል።

- ፈርዖን የተናገረውን እስቲ እንመልከት፡

ዘጸአት 14፡5-9

5- የግብፅ ንጉሥ ሕዝቡ መሄዳቸው በተነገረው ጊዜ፣ ፈርዖንና ሹማምንቱ ስለ እነርሱ የነበራቸውን አሳብ በመለወጥ፣ «ምን ማድረጋችን ነው? እስራኤላውያንን እንዲሄዱ ለቀቅናቸው፤ አገልግሎታቸውንም አጣን» አሉ።

6- ስለዚህ ፈርዖን ሠረገላው እንዲዘጋጅለት አደረገ፤ ሠራዊቱንም ይዞ ተንቀሳቀሰ።

7- ስድስት መቶ ምርጥ ሠረገላዎችን፣ ከሌሎች የግብፅ ሠረገላዎች ጋር ከነጦር አዛዦቻቸው አሰልፎ ተነሣ።

8- እግዚአብሔር የንጉሡን የፈርዖንን ልብ ስላደነደነው በልበ ሙሉነት ከግብፅ የሚወጡትን እስራኤላውያንን አሳደዳቸው።

9- ግብፃውያን ይኸውም የፈርዖን ፈረሶችና ሠረገላዎች፥ ፈረሰኞችና እግረኞች ሁሉ እስራኤላውያንን አሳደዷቸው፤ በበአልዛፎን አንጻር በባሕሩ አጠገብ በፊሀሒሮት ሰፍረው ሳሉ ደረሱባቸው።

- ፈርዖን እስራኤላውያንን መልሶ ለመያዝ ያስብ ነበር።

- ስለዚህም ፈርዖን ጦሩን አሰባሰበ እስራኤላውያንንም መልሶ ለመያዝ ሄደ።

- ፈርዖን እስራኤላውያንን መልሶ እንዲይዝ ይመራው የነበረው ማን ነበር?
- ሰይጣን።

- ሰይጣን ፈርዖን መልሶ እስራኤላውያንን እንዲይዝ የፈለገው ለምን ነበር።
- ሰይጣን እስራኤላውያንን ሊያጠፋ ስለ ፈለገ።

- እስራኤላውያን ፈርዖንና ጦሩ መልሰው ሊይዟቸው እንደ መጡ ሲያዩ ምን አደረጉ?

ዘጸአት 14፡10ሀ & 11-12

10- ፈርዖን በቀረበ ጊዜ፣ እስራኤላውያን ቀና ብለው ተመለከቱ። እነሆ ግብፃውያን ይከታተሏቸው ነበር፤

11- እነርሱም ሙሴን እንዲህ አሉት፤ «በምድረ በዳ እንድንሞት ያመጣኸን በግብፅ መቃብር ቦታ ጠፍቶ ነውን? ከግብጽ አውጥተኸን ምን አደረግክልን?



12- በግብፅ ሳለን፣ ተወን እባክህ፣ ግብፃውያንን እናገልግል አላልንህም ነበርን? በምድረ በዳ ከምንሞት ግብፃውያንን ብናገለግል ይሻል ነበር!።»

- እስራኤላውያን ሙሴን ነቀፉት በግብፅ መቆየት ይሻላቸው እንደ ነበረ ነገሩት።

- እግዚአብሔር አሥሩን መቅሰፍቶች በግብፅ ምድር ላይ አውርዶ ቢያዩም እንኳን እስራኤላውያን አሁንም በእግዚአብሔር አላመኑም ነበር።

- እስራኤላውያን በእግዚአብሔር ባያምኑም ሙሴ ግን ያምን ነበር።

- ሙሴ ለእስራኤላውያን ያላቸው ይህን ነበር፡

ዘጸአት 14፡13-14

13- ሙሴም ለሕዝቡ መለሰላቸው፤ «አትሸበሩ፣ ጸንታችሁ ቁሙ። እግዚአብሔር ዛሬ የሚያደርግላችሁን መታደግ ታያላችሁ፤ ዛሬ የምታዩአቸውን ግብፃውያን ዳግም አታዩአቸውም።

14- እግዚአብሔር ስለ እናንተ ይዋጋል፤ እናንተ ያለባችሁ መታገሥ ብቻ ነው።»

- እስራኤላውያን ራሳቸውን ማዳን ችለው ነበር?
- አልቻሉም።

- እስራኤላውያን ራሳቸውን ማዳን ያልቻሉት ለምን ነበር?